*Salale Journal of Social and Indigenous Studies Volume I issue II February 2025*

**Original Research in Amharic**

# ፍካሬ ፍቅር ወአንድነት/ዘፖለቲካ/ በአደፍርስ

Pawlos Zemariam[1]


## *አኅጽሮተ ጥናት*

*“አደፍርስ” ከቅድመ አብዮቱ መባቻ ልብ ወለድ መኻል አንዱ ነው፡፡ይህ ልብ ወለድ ዐያሌ የነገረ ሰብእ ጉዳዮችን በውስጡ አምቆ የያዘ “ዘመን ተሻጋሪ” ልብ ወለድ ነው፡፡ይህ ጥናት ከዚህ ልብ ወለድ የንባብ አሐዶችን መርጦ በመውሰድ ማኅበረ ለፖቲካ ሒሳዊ ንባብ ማቅረብን ዐቢይ ዐላማው አደርጓል፡፡ምርምሩ በቴክስታዊ የንባብ ሐዶችን እየታገዘ ከማኅበረ– ፖለቲካዊ እስቦች አንጻር አሐዶችን ፈክሯል፡፡ በጥናቱ ሂደት ውስጥም ቴክስታዊ አሐዶችን የመለየት፣ የማጣመር፣ የማዋቀር እና የመለወጥ ሒሳዊ የንባብ ደረጃዎች ተከናውነዋል፡፡ዋና ሥልቱ ግን ፖለቲካዊ አንድምታና ፍካሬን ማቅረብ ነው፡፡ ዐዲሱየታሪክ ሥነ-ጽሑፋዊ ሂስ ንድፈ ሐሳብን በመከተል በመቼቱ ኹነት፣ በገጸ ባሕርያቱ ተዋሥዖ እና በኪነታዊ ሥነ-ጽሑፍ ሥልቱ ውስጥ ኹለንተናዊ ፍካሬን ለማቅረብ ሞክሯል፡፡ምርምሩ ዐይነታዊ አንጻር ተከትሎ በጥብቅ ሒሳዊ ንባብ ተካኺዷል፡፡ ርእዮተ ዓለማዊ መሻቶችና ቅራኔዎች ከተውኔታዊ ድርጊቶች ተጣጥመው በልብወለዱ ትልማዊ ጉዞ እስከ መጨረሻ የማይፋቱ ጉዳዮች ናቸው:ስለዚህም በድርሰቱ ውስጥ ፍቅርና አንድነት፣ የለውጥ ፍላጎት ማኅበራዊ ተሐድሶና ግለሰባዊ እሳቤ እርስበርስ ተጋምደው የቀረቡ ጭብጦች ናቸው:: በዚህም ውስጥ የብሔረ መንግሥት ግንባታውእውን የሚኾንባቸው ፍቅርና አንድነት ሠምረውና አብረው ዐቢይ ጭብጥነት ግዘፍ ነሥተው ቀርበዋል::*


**ቁልፍ ቃላት፡***አደፍርስ፣ “ዘመን ተሻጋሪ”፣ በቴክስታዊ የንባብ ሐዶች፣ ሥነ-ጽሑፋዊ ሂስ ፣ተውኔታዊ ድርጊቶች*

[1] MA. In Folklore and Literature, Salale University

## ፍካሬ ፍቅር ወአንድነት/ዘፖለቲካ/ በአደፍርስ ፲፪ ምዕራፍ

The last end of the state is not dominate men, nor to restrain them by fear rather it is so free each man form fear that he may live and act with full security and without in jury to himself or his neighbor. The end of the state I repeat is not to make rational beings in to brute beasts and machines.It is to enable their bodies and minds to function safely.It is to lead men to live by, and to exercise,a free reason;that they may not waste their strength in hatred,anger and guile,nor act unfairly toward one another.Thus the end of the state is really liberty/Spinoza in story philosophy by will Durant p. 46/

### መግቢያ

በዚህ መጣጥፍ "አደፍርስ" በተባለው ልብወለድ ውስጥ ዐያሌ የነገረሰብእ ዕስቦች የሚነሡ ቢሆንም በረቂቁ የተሣለውን የዘመኑን መንፈስ መንደፍ እና ማሳየት የዚህ ጥናት ዐቢይ ዐላማ ነው፡፡ በዚህ ፖለቲካዊ ሐቲት ጥናቱ በልብወለድ ብቻ የተገደበ መሆኑ መግለጥ እሻለሁ፡፡ ቅኝቴም በዘመን ቅደም ተከተል ፈር የተሰደረ ሳይሆን በድርሰቱ ይዘት ውስጥ ሥግው ሆኖ የቀረበ ነው፡፡ ትኩረቱም በቅድመ አብዮቱ ዋዜማ የተከሠቱት ክስተቶች በማኅበሩ ልቡና ላይ ያላቸውን ጫና እና በመጻኢው ላይ የሚወሰዱትን ሚና ይፈትሻል፡፡ ስለዚህም በዚህ ንኡስ ርእይ ምን ዐይነት መንፈስ፣ እንዴት ባለ ሁኔታ እንደተነደፈ በስሱ በፍካሬ አሳያለሁ፡፡ዚህም የደራሲውን በሉ፣ የማኅበሩን፣ ብሎም የትውልዱን የመንፈስ ዓለም ለማመልከተ ተሞክሯል፡፡ ዘመኑን በገቢር እና በርእይ ባላወቀውም በድርሰቱ ውስጥ የተነሡትን ቁም ነገሮች ነቅሶ በማውጣት አንዳች ቁም ነገር ለማትረፍ ይህ ጎዳና ተመርጧል፡፡ ለዚህም ሲባል ቴክስታዊ የፍካሬ ጎዳና መፈከርያ መሣሪያነት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

ይህን ካልኹ ዘንድ ወደ ዋናው ጉዳይ ላምራ፡፡ ሥነ-ጽሑፍ በኹሉም ዘንድ በሚታወቀው ግብሩ የተጻፈበትን ዘመን አጎልቶ የሚያሳይ መስታወት ነው፡፡ በገሀድም በረቂቅም መንገድ

ይህኑ ግብሩን ይወጣል፡፡ በዚህም የደራሲውን የፖለቲካ አቋም እናይበታለን፡፡ በተለይም ከታላቅ ተመስጣ የተወለዱ ትንቢታዊነት የማያጣቸው እንደ "አደፍርሰ" ዐይነት ልብወለዶች ያለፈውን ያረቃሉ፤ መጻኢውን ይተነብያሉ፤ ነገን በገሃድ ያሳያሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ዳኛቸው ወርቁ የኢትዮጵያ ማኅፀን ካፈራቸው ድንቅ አሳቢዎች መኻል አንዱ ነው፡፡ ይህ ደራሲ በአብዮቱ መባቻ ሲከሠቱ የነበሩትን ማኅበረ ፖለቲካዊ ቀውሶች በአግባቡ አጢኖ፤ አማራጭ የፖለቲካ መፍትሔዎችን ካመለከተበት ኪናዊ ሥራዎች ውስጥ በዋናነት አደፍርስ ተጠቃሽ ነው እላለሁ፡፡ እኔም በዚህ ግዙፍ ድርሰት ውስጥ በ፲፪ኛው ምዕራፍ ላይ በተገለጸው አንድ ኹነት ላይ ተመሥርቼ እንደ አስፈላጊነቱ ከድርሰቱ አካል ከምወስዳቸው የተለያዩ ኹነቶች ጋር አዛምጄ ፍካሬዬን አኼዳለሁ፡፡

መግቢያ ላይ እንደ መሪ ቃል የተገለገልኩበትን የፈላስፋውን ባሮክ ሲፒኖዛን ብሂል በነፃ የትርጉም ስልት ወደ አማርኛ ብቀዳው የሚከተለውን ይመስላል፡፡ የሀገረ መንግስት ዋና ጉዳይ ዜጎችን በፍርሃት ማሸማቀቅ፣ መጨቆን ሳይሆን ተደላድለው ያለ ፍርሃት እንዲኖሩ ማስቻል ነው፡፡ እደግመዋለሁ የሀገረ መንግስት ዐቢይ ተግባር ለባዊውና ለስላሳውን ሰብኣዊ ፍጡር ተናካሽ ተኩላ እና ግዑዝ ማሽን ማድረግ አይደለም፡፡ እኔም በበኩሌ ከዚህ ከፈላስፋ ብሂል ጋር ተስማምቼ፣ የጽሑፌ መሠረት የኾነው አደፍርስ በብዙ ሁኔታ ከፈላስፋው ብሂል ጋር ገጥሞ አግኝቼዋለሁ፡፡ ከዚህ ሐሳብ በርእሰ ጉዳይነት የሚወጡ ርእዮተ ዐለማዊ ሐሳቦች ይረቃሉ፡፡ ትንታኔውም በፍካሬ መንገድ ላይ ስለተመሠረተ ፖለቲካዊው ርእዮተ ዐለም ከተለያየ አቅጣጫ በተለያየ መንገድ ይፈትሻል፡፡ ሐቲቱም ከተነገረው ጀርባ ያለውን ትርጒም እና አንድምታ እማውጣት ላይ ትኩረትን ያደርጋል፡፡ ለዚህ ተግባራዊ ሲባል ለጽንሰ ሐሳቡ ማኼጃ እና ማኅልመሻነት "ፖለቲካዊ ሒስ" ከ "ፍካሬ" ኀዳና ጋር ተዛምዶ ቴክስቱትን ለመተንተን አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

በድርሰቱ ፖለቲካዊ ሒስ ከማቅረቤ በፊት በዚህ የድርሰት ሥራ ላይ የተሠሩ ቀደምት ምርምሮች መመልከት ተገቢ ነው፤እነዚህንም በሁለት ወገን ወግኖ መቅረብ ይቻላል:: አንደኛው ወገን ልብወለዱን ከሌሎች የአማርኛ ልብወለዶች ጋር በንጽጽር ወሰደው የዳሰሱ ሲሆኑ፤ሁለተኛው ልብወለዱን እራሱን አስችለው በውስጡ የተነሡትን ርእሰ ጉዳዮች የመረመሩ ናቸው:: በመጀመሪያው ጎራ የተሰለፉት ሥራዎች በዋናነት ካነሧቸው ነጥቦች መኻል ፊውዳሊዝም ፣ማኅበራዊ ልማድና እይታ ተጠቃሽ ናቸው:: በሁለተኛው ጎራ ከተነሡ ጉዳዮች መኻል ከቴክኒክ አንጻር የገጸባሕርያት ግጭትና ጭብጥ ፣ዘይቤ ፣ምሳሌያዊ ንግግርና ስልት ይገኛሉ::ከእነዚህ የምርምር ሥራዎች ተጨማሪ በሥነጽሑፍ የምርምር መጽሔት የታተሙ ሌሎች ሁለት

ሥራዎች ይገኛሉ:: የመጀመሪያው ሥራ ፈቃደ አዘዘ በአደፍርስ የመጀመርያ ምዕራፍ የገለጻና የምልልስ ፋይዳ ላይ ያቀረበው ነው ። ፈቃደ በዋናነት በቀዳሚው ምዕራፍ የተለየ የመልካ ምድር ገለጻና የምልልሱ ሚዛነ ቢስነት ከፊውዳሊዝም ኹነታ በማገናኘት ከቴክኒክ አንጻር ምን አይነት ፋይዳ እንዳላቸው ለማሳየት ሞክሯል:: ነገር ግን ዐቢይ ትኩረቱ የቴክኒክ ፋይዳ በመሆኑ የመቼቱን ርእዮተ ዓለማዊ አንድምታ በምርምር ሥራ አልዳሰሰም:: ሁለተኛው ሥራ በቴዎድሮስ ገብሬ የቀረበ ሲሆን ሥራው አደፍርስ ዘመናዊ ልብወለድ መሆኑን የሚፈትሽ ነው:: ዘመናዊ ልብወለድ ነው ለማለት የሚያስችሉ መስፈርቶችን በድርሰቱ ውስጥ የተነሡ አንኳር ጉዳዮችን፣ የተመሠረተባቸውን ጽንሰ ሐሳቦች፣ ያተኮረባቸውን ቴክኒኮችና ዘይቤዎች ነቅሶ በማውጣት አሳይቷል:: ቴዎድሮስ በበኩሉ አደፍርስ ዘመናዊ ልብወለድ መሆኑን ሲያጠይቅ ሥነልቡናዊ፣ ሥነማኅበረ ሰባዊ፣ ፍልስፍናዊና ኪነጥበባዊ ዕሴቶች ተጣጥመው የቀረቡበት የጎልዮ ልብወለድ መሆኑን ያነሣል:: ነፃ ቅንጂትና እንደ ወረደ ከሥነጽሑፋዊ ብልሀት ባሻገር ለፍርቅነትና ለባይተዋርነት ማግዘፊያ እንዴት እንደዋሉ ከድርሰቱ በተወሰዱ ማሳያዎች ማንጸሪነትያቀርባል:: ሌላው ቴዎድሮስ ያነሣው አንኳር ነጥብ “ምልልሱ” ገጸ ባሕርያቱ የወጡበትን ኹነት በማሳየት አለመወሰኑን፤ በሂደትም የአንድን ማኅበረሰብ ውቅርና የውቅሩን ዕጣ እንደሚያሳይ ይናገራል:: ይህም ምርምራዊ ጽሑፍ ይህን ሐሳብ እንደ አንኳር ነጥብ ይዞ ማኅበረ ፖለቲካውን ይመረምራል::ቴዎድሮስ በምርምራዊ መጣጥፉ ውስጥ የአባ ዮሐንስ ዋነኛ ትኩረት “የአገር አንድነት፣የአገር ነፃነት” ነው በማለት ከአደፍርስ አንጻር ግብራቸውን በአወንታ ጎን ያነሣል:: ከአደፍርስ አውቅላችኂለው ጋር የእሳቸውን ማን ያውቃል? በማለዘብ በንጽጽር በመጥቀስ አባ ዮሐንስ የሚናገሩትን ያውቃሉ፤ በማለት የፀረ ባይተዋርነት ማእምር አድርጎም ያቀርባቸዋል::እኔግን በበኩሌ አባዮሐንስ በተመለከተ ከቴዎድሮስ የተለየ ሐሳብ ነው ያለኝ:: አደፍርስም ሆነ አባዮሐንስ የትይዩ ዓለማት አቻ ገጸሰብ ናቸው::አንዱ የትምህርት አፋዳሽ ሌላው የሃይማኖት አፋዳሽ:: በእርግጥ አባዮሐንስ የሚናገሩትን ያውቃሉ? ስሙኝ ልንገራችሁ አይበሉን እንጂ የአንድነትና የነፃነት ንግግራቸው ስብከት አከል ነው:: ለዚህም በማኼደው ፍካሬ ከአንድም ሁለት ማሳያ ከልብወለዱ ወስጄ አሳያለሁ ። አባ ዮሐንስ በርግጥ መዋጮ ጥለዋል እውነት ወይስ ምፀት? የምስጢር ቤት ልመናውስ? እንዴት ይታያል:: በዋናነት የቴዎድሮስ ሥራ የዘመናዊ ልብወለድ ነቁጦችን ከድርሰቱ ክፍሎች በማውጣት ኪናዊ አንድምታን መተንተን ላይ ያተኮረ ነው እንጂ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ የተከማቸውን ፖለቲካዊ አንድምታ ማኼድ አይደለም:: እኔግን የድርሰቱ ማእከለ ነጥብ ዐሥራ ሁለተኛው ምዕራፍ ይመስለኛል:: ለዚህም በድርሰቱ ውጫዊ ክፍል የምናገኘው ሥዕላዊ መግለጫው አንዱ ማሳያ ነው ። ሌላው የጊዜና የስፍራ ጥምረት በመፍጠር በአንድ ቅጽበት ሦስት የተለያዩ ኹነቶችን ተጎራብተው መቅረባቸው ነው::

በድርሰታዊ ሥራ ላይ ስለ ተሠሩ ምርምሮችና ስለድርሰቱ ጥቅል ገጽታ እነዚህን ውስን ነጥቦች ካነሣን ወደድርሰቱ ፍሬ ነገር እናምራ:: “በአደፍርስ” በመግቢያ መቼት ውስጥ የሚያጋጥመን ሕይወት ያበቃለት እና ያከተመ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህም ኹነት የመንፈስ መበስበስ እና መፈራረስ በሚያሳይ መልኩ አቧራ በረጋበት ሜዳ ተወክሎ ቀርቧል፡፡ ኹለቱ የዐዋዲ እና የጀውሃ ጅረቶች በጥንታዊት መሰጸጣሚያ አምሳል

የጥንታዊ ሥልጣኔ ትእምርቶች ቢሆኑም የደም ወንዝ እና የትግል ዐውድ ኾነው ተሥለዋል፡፡ አፍላጋቱ የታላቋ ኢትዮጵያ ንኡሳን ምስሎች ናቸውና የአማራው፣ የአርጐባው፣ የአፋሩ እና የኦሮሞው መፋለሚያ ኾነው ቀርበዋል፡፡ እነዚህ በመቼትነት የቀረቡልን ጉብታዎች ክብር እና ልዕልናን ሳይኾን የእየ ዘመናቱን ችግር እና መከራ የሚፈክሩ ናቸው፡፡ ጉብታቸው ላይ ላይ ታቦታት ቢተከሉም በእነዚህ ስፍራዎች የመንፈስ ሥርዓት ገና አልሰፈነም፤ለዝንተ ዓለሙ የሚሰፍንም አይመስልም፡፡ ይህ ስፍራ እውነትም ጣር-በር ላይ ኾነው ሲያዩት የዘመናት ትርክምክም የታጐረበት ዕቃ ቤት ነው፡፡ ዕቃ ቤትነቱም በውስጡ የሚገኙት ነዋሪዎች ወደ ግዑዝነት ዕቃ የሚለውጥ፡፡ እነዚህ እግዜር ያስቀመጣቸው ቁርጥራጮች እጅ ሥራዎቹ መኾናቸው ችግሩን የተፈጥሮ ያህል ጸናን ያደርገዋል፡፡ የበዓላቱ ጋጋታ እና የቅዱሳኑ መንፈሳዊ ዕሴት ነዋሪውን በክብር ዕሴት አላስጌጠውም፤ ከመከራው እና ከስቃዩ አልታደገውም፡፡ በዚህ ዓለመ ልቡና ውስጥ የሕይወት ግብ እና ፈለግ በድግግሞሽ እና በተራ ጉዳዮች የተሞላ ነው፡፡ሕይወት በጥንተ ተፈጥሮዋ ዕርቃኗን የምትጓዝበት ጎዳና ላይ ቆማለች::

የይፋትና የጥሙጋን አውራጃ ጣርማ በርላይ ሆነው ተራራ ላይ ሲመለከቱት እግዚአብሔር ዓለሙን ሠርቶ ሲያበቃ የቀረውን ትርክምክም ያጐረበት ዕቃቤቱ ይመስላል:: ሸለቆ ፣ጉባው፣ተራራው ፣ገመገሙ፣ጭጋጉ ፣አቢራው ሕይወትን አፍኗት ተኝታለች:: ያቺ በሌላው አገር የምትጣደፈው የምትፍለቀለቀው የምትንቦለበለው ሕይወት እዚህ እፎይ ብላለች__ በርጋታ ፣በዝግታ ታምማለች፤በተገማሸረ መስክ ውስጥ እንደ ሚብሰከሰክ ውሃ….(አደፍርስ፤ ገጽ፣5)

ይህ ዓለመ ሰብ የሕይወት እና የመንፈስ ህላዌ የተገለባበጠበት ነው፡፡ እነዚህ መልክአ ምድራዊ መባያዎች ለአያሌ ዘመናት የባከነና የዳሸቀውን ማኅበረ ህላዌና ከዚህም ጋር የተሳሰረው ሥርዐተ መንግሥትን ይተረጉማሉ::ሂደቱ ከጥታዊት ኢትዮጵያ እስከ ዘመናዊት ኢትዮጵያ የሚዘልቅ ነው::

ኢዛና__ ዐምደ ጽዮን __ዘርዐ ያዕቆብ __ሱስንዮስ__ አምኀየስ__ አብዬ መሳፍንት__ ዮሐንስ___ ቴውድሮስ__ ምኒልክ __ደለሏን ትጥለዋለች__ አዝብጤ __ጫልቱ__ ለጴሳ__ ጉንጤ__ ሐዳስ__ ቀመሩ__ አዛለች_ ወርደፋ__ አርያም__ ጨቡዴ __አያንቱ__ ገብሬ__ ተዋበች __ነስሩ__ መገርቱ__ ቢራቱ__

> ለተሚካኤል__እርገጤ__ አያንቱ __ሐጐስ __ኩሬ ___ጉድባ __ጉድባ __ኩሬ__ __ክትር__ ክትር__ ጉድባ__ ጉድጓድ__ ኩሬ__ ክትር__ ጐለንታ__ መስኖ__ በርጋታ__ በዝግታ __ትፈሳለች __በሌላው አገር የምትጣደፈው __የምትፍለቀለቀው__ የምትንቦለበለው ይችው ሕይወት…..(ገጽ፣6)

ይህን መልከአ ምድራዊ መቼት የኢትዮጵያ ንኡስ ምስል አድርገን ፈክረናልና ከኢዛና (ከቀዳማዊቷ አክሱማዊት ኢትዮጵያ) እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመናዊት ኢትዮጵያ ድረስ ያለውን ፖለቲካዊ ምስቅልቅል በመልክአ ምድሩ ማንጸሪያነት የሩቁ ቀርቦ፣ ረቂቁ ገዝፎ ይታየናል፡፡ ይ የሀገረ መንግሥት ሥዕላዊ መልክአ ምድር አቀማመጥ አሰደናቂና አሰገራሚ ነው።ለዚህም ማሳያ መጥቀስ እንችላለን።በቀረበል የንባብ አሐድ ውስጥ "ምኒልክ __ ደለኋን ትጥለዋለች"፡፡የሚል ብሂል ያጋጥመናል። ይህ እንደ ዋዛ የተወረወረ ብሂል የዘመናዊት ኢትዮጵያ ችግር፣ የየዘመናቱ ብካች እና ምስቅልቅል ማረፊያ አፄ ምኒልክ መኾኑን ያጠይቃል፡፡ ከላይ ከኢዛና የጀመረው የሀገረ መንግሥት ግንባታ ፈር የያዘው በአፄ ምኒልክ ነው፡፡ ከምሥረታው በኋላ ቢኾን ደለሉ ፣ ረግረጉ እና ጮቄው የሚያራምድ እና የሚያሳልፍ አይደለም፡፡ ስለዚህ ይመስለኛ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ በተነሣ ቁጥር አፄ ምኒልክ ኹሌም ማጠየቂያ የሚኾኑት፡፡ ደራሲውም ይህን የዘመናት ውርስ ችግር ትብ በኾነ ብዕሩ በቅጡ ያመላከተ ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ታሪካዊ ኹነት የተነሣ በአንድ በሌላ መልኩ በየአቅጣጫው የታሪክ ዲስፕሊን እጁን ተጠምዞ ለፖለቲካዊ መሻት መሣሪያ ኾኖ ሲቀርብ ያጋጥመናል፡፡ ከዚህ ኹነት በታች የተከተበልን የስም ዝርዝር "የብሔር ብሔረሰቦች የኢትዮጵያን" የሚያሳይ የሚወክል ምስል ይመስላል፡፡ የቀረበልን ዓለም ግላዊነት የሰፈነበት እና ማኅበራዊነት የተመናመነበት ነው፡፡ ስለዚህም ከአዝብጤ ጋራ ስንዘብጥ፣ ከሌጴሳ (ልባችንን ሲታመም)፣ ከጎንጤ ጋራ እርስ በርስ ስንጓነጥ፣ ከሐዳስ ጋራ እራሳችንን እንደ ታደስን ስንቆጥር እናገኘዋለን፡፡ ይህን አጣጥመን ሳናበቃ ከአዛለች ጋር እንዝላለን፤የስሞቹ ዝርዝር ይህንኑ ማኅበረ ፖለቲካ የሚያስተረጕም ነው ፡፡ የደለሉ ራስጌ ተናጠላዊ እኔነት ሲኾን ግርጌው ደግሞ ኩሬ፣ ጉድባ እና ክትር የበዛበት ጽልመታዊ ዓለም ነው፡፡ ይህ ምስል ኅብረ ብሔራዊነት ያላበበባትን "ብሔረሰባዊት ኢትዮጵያ" ይወክላል፡፡ መልክአ ምድሩ ይህን የሚመለከት መባያ ጭምር ነው፡፡ የክትሩ እና የጉድባው ብዛት የማኅበሩን በአብሮነት አለመዘመን እና አለማበር የሚጠቁም ነው፡፡ በፍጻሜ ጀውሃ ጅረትነቱ አብቅቶ "የታቆረ ውሃ" ከዚያም በመስኖነት ሥራውን የሚጀምር ምንጭ ይኾናል፡፡ ምናልባትም "መስኖው"

በቀደምት የአማርኛ የነገሥታት የውዳሴ ግጥም ውስጥ የንጉሥ ዓምደ ጽዮን ድል አድራጊነት መመሰያ ኹኖ ቀርቧል::

ሐርበኛዓምደ ጽዮን

መላላሽ የወሰን

ውሃ እንደመስን ተመላላሽ የወሰን::(አምሳሉአክሊሉ፤አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ቅኝት፣47 "መስኖ" በውዳሴ ግጥሙ የሀገረ መንግሥት ግንባታው ትእምርት ኹኖ እንደ ቀረበ ኹሉ የመጻኢዋ ምድረ ገነት፣ የተስፋዋ ምድር ኢትዮጵያ የጋራ እድገት እና ርእይ የሚጠቁም ትእምርት ነው ማለት እንችላለን፡፡ እስከ መጻኢው ተስፋ ድረስ በዚህ ምድር ነው፤ የወዘሮ አሰጋሽ ረጅም ዲስኩር እና የምስኪን ገበሬው መቆራመት የምንሰማው እና የምናየው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ የወረደፋ ዋሽንት የሚስረቀረቀው፡፡ በርግጥም በዚህ ምድር ውስጥ ነው፤ ከራሱ ጋር የተጣላው ገጸሰብ አደፍርስ የሐሳብ ጋጋታን የሚያዘንበው፡፡በዚህ ምድር ውስጥ ነው፤ በየዐይነቱ አፋዳሾች የሚራኮቱበት፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፤ ሕይወት እና ሞት፣ ዕውቀት እና ድንቁርና ሥልቱ ስቶ የሚቀላቀልበት፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፣ የፌንጣ እና የእንቁራሪት ስርስርታ እና ቁርቁርታ ሰላማዊውን አየር የሚበክለው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ጥራዝ ነጠቅ ሥልጣኔ እና አጎራ ዘለልነት የሰፈነው፡፡

በዚህ ዓለም ማኅበር ውስጥ ነው፤ ጽዮኔ ለገዳም ሮማን ለቡና ቤት ሕይወታቸውን የሚገብሩት፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ልቡሰ ሥጋ ከቁርጥራጭ ወረቀት ተቀስሞ የነዋሪው ሕይወት በክ የሚያደርገው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፤ አንድነት እና ፍቅር የሚታዩ እንጂ የማይበሉ ፍሬ የኾኑት፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፤ የበላይ ሕልማዊ ቅዥት እና ጭራቁ ተረት እውናዊነትን ተለብሶ የሚተረከው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፤ሞት "ሞትና ሕ.ይ.ወ.ት ድንቁር…" ገዝፈው ተጽፈው ድንቅ ድንቁርና የሚኾኑበት፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፣ እንደ አቶ ጥሶ ያሉ ሀገር ወዳድ ተራማጅ ገጸሰብ ሕይወታቸው ባክኖ የሚቀረው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ እኮ ነው፤ የአባ ዐዲሴ እና የአባ ዮሐንስ የመንፈስ ጽናት ሕዝቡ አንገቱን ማቃናት የተሳነው፡፡ በዚህ ምድር ውስጥ ነው፣ እንደ አደፍርስ ባሉት ተስፈንጣሪ የሕዝቡ የመንፈስ እና የእምነት ዓለም የሚበረዘው፡፡ በዚህ የልብወለድ መቼት የልብወለዱን ተፋሰሶች ከቃኘን በዋናነት ለፖለቲካዊ ሐቲት ወደ መረጥሁት ምዕራፍ ፲፪ እናምራ፡፡

## መክብበ ነገር

በቀዳሚ ድርሰቱ መግቢያ ክፍል ላይ በመቼትነት የቀረበልን ተፈጥሯዊ የመልክአ ምድር ገለጻ ይገኛል፡፡ የዚህ ኹሉ መልክአ ምድር ዋና ሐሳብ “ጣርማ በር ላይ ኾነው ሲያዩት እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጥሮ የቀረው ትርክምክም ያኖረበት ዕቃ ቤት ይመስላል” በሚለው ሐሳብ ተጠቃሎ ተነግሮናል፡፡ ከላይ ይገፔ በተነሣሁበት ፖለቲካዊ ፍካሬ አተያይና በድርሰቱ ኹለንተና ውስጥ በተዘረዘሩት በነገረ ሰብእ ጉዳዮች አንጻር ይህ መልክአ ምድራዊ ገለጻ ተፈጥሮን አይከሥትም፡፡ ቀረበልን መልክአ ምድራዊ ገለፃ ትይዩ እይታችንን ወደ ዓለመ ሰብኣዊ መልክአ ምድር ስንመልስ ከውጪ ወደ ውስጥ ስንመለከት “ትርክምክሙ” እና “ዕቃ ቤቱ” የነገረሰብእ ጉዳይ ሆኖ ይታየናል፡፡ ይህ “ዕቃ ቤት”እኔ ማነኝ? ምድንስ ነኝ? ዕቃ የበሰበስኩኝ ዕቃ ከሚለው ከአበራ ወርቁ ሁኔታ ጋር የሚናበብ ሕይወት ነው ፡፡ በአንዳች ሁኔታ ሥርዐት ወዳለው ቤት /ወደ ሳሎንነት/ አይለውጥም፡፡ በአንድነት ኹሉ ወደሚያሰባስብ አደራሽነት አያድግም፡፡ ሥሪቱ የተፈጥሮ ያኽል የጸነነ ነው፡፡ እዚህ ላይ የቀረቡልን የተቆራረጡ መልክአ ምድሮች፣ ሸለቆው፣ ጉባው፣ ተራራው፣ ገመገሙን ከማኅበረ ፖለቲካዊ ርእይ አንጻር አስተውለን ስናጤናቸው በሀገሪቱ ታሪካዊ ጉዞ ውስጥ ባለፉት ሥርዐተ መንግሥታት ያልተደላደለ የማኅበረሰቡ ህላዌ ማደሪያ ናቸው፡፡ ተግባራቸውም ውበትን፣ ተፈጥሮ መከሠት ሳይሆን ሕይወት ማፈን፣ መጫን፣ መጨገግ ነው፡፡ በእነዚህ ተራራዎች ውስጥ የሰማይ ስባሪ አከል ችግሮች የተጫናት ሕይወት በእይታችን ፊት ቀርባልናለች፡፡ በጀውሃ እና በዓዋዲ ጅረቶች ትይዩ የምትፈሰዋ ሕይወት በቅርጽ ፍርቅርቅነት በዘልማዱ ሕይወት ውስጥ ትከሠታለች፡፡ በዚህ ሐሳብ መሠረት መልክአ ምድሮቹ በየዘመናቱ የተከሠቱ ማኅበረ ፖለታካዊ ምስቅልቅሎች ሥግው የኾኑባቸው ግዘፍ የነሡባቸው መከሠቻዎች ናቸው፡፡ ይህንኑ ሐሳብ ያመላክቱናል፡፡ በኹለቱ ወንዞች መኻል (እንደ ጥንታዊቷ የስልጣኔ መነሻ መሰጾጣሚያ) እንደተወጠነው ስልጣኔ ማኅበረ ፖለቲካዊ የሕይወት ጅረት እያደር ይቀንሳል ቀስ በቀስ ወደ መልካነት ይለወጣል፡፡ እነዚህን ጅረቶች ከግእዝ አቻ ቃል “ፈለግ” ጋር አጣምረን ወደ “ጉድጓድነት” መለወጣቸው ጋር ስናናብበው በማኅበረ ፖለቲካ ሥርዐት ውስጥ “ፈለግ” መሳት ዐቢይ ችግር መኾኑን ያስተረጉመናል፡፡ በድርሰቱ መግቢያ ላይ የቀረበልን የሥርዐተ መንግሥታት መፈራረቅ ዑደት ገለፃ ከዚሁ ኹነት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ “ኢዛና… ምኒልክ ደለሏን ትጥለዋለች፡፡” ከጥንታዊቷ አክሱማዊት ኢትዮጵያ

(ኢዛናዊቷ) እስከ ዘመናዊቷ ኢትዮጵያ (ምኒልካዊቷ) ያለውን የሥርዐተ ፖለቲካ ምስቅልቅል ቅርጽ ማያዝ አለመቻሉን በተራራዎቹ መተርጐሚያነት እንረዳለን፡፡

ይህ የተመሰቃቀለ መልክአ ምድር የትርክምክም መደብር ነውና ፍቅር እና አንድነት የሚገናኙበት ዓለም አይደለም፡፡ “ምኒልክ” በዚህ መልክአ ምድራዊ ገለጻ እንደ ጅረቶቹ ዳርቻ ደለል መጣያ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ይህ ገለፃ የዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መንገድ ጠራጊ መሪ ፊት የተደቀኑትን ውስብስብ ፈተናዎች አመልካች ነው፡፡ እንዲሁ በይደር እንያዘው እንጂ የየዘመናቱ ሥርዐተ ፖለቲካዊ ብካች መጣያ፣ የየዘመናቱ እድፍና ቆሻሻ ማራገፊያ የመሆኑ አንድምታ ብዙ አሳስቦ ብዙ ያናጋራል፡፡ ይህን የደለል ዳርቻ የየዘመናቱን ሥርዐት መገልማት፣ የየዘመናቱን ታሪካዊ ስሕተቶች (የፍቅርና የአንድነት መመናመን) አቅርቦ በማደሪያነት ያሰተረጕማል፡፡ መልክአ ማኅበረሰባዊ ዓለም በአንድም በሌላም መልኩ (ፍቅርና አንድነት ወደሚገለጥበት) ተፈጥሯዊ ውበት አይሻገርም፡፡ ውበትና ሕይወት አብበው አያፈሩበትም ይረግፉበታል ብካች ይሆኑበታል እንጂ፡፡ በቀጣይ ከ“አዝብጤ… እስከ ሐጐስ” በቀረበልን ገለጻ አዝማነ ነገሥት  በአዝማነ ግለሰቦች መተካቱን፣ አንድነት ለተናጠላዊነት ስፍራውን መልቀቁን ያመላክታል፡፡ ስለዚህ በጅረቶች ዘመን ፍጻሜ መልክአ ምድሩ “በኲሬ በጉድባ በክትር” መተካቱ ከፍቅርና ከአንድነት ወደተናጣላዊ ምስቅልቅ የሚያመራ ማኅበረ ፖለቲካዊ ቀውስ ውስጥ መግባታችንን ማሳያ ነው፡፡ በጥቅሉ እነዚህ የመልክአ ምድሮች አቀማመጥ የማኅበረሰቡ መልክአ ልቡና መበጣጠስ፣ መቆራረጥ፣ ገደላማት ማንጸሪያ ናቸው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደቀረበልን ተምሳሌታዊ ትረካ ደኻው በአብርሃም ዕቅፍ ሆኖ ሀብታሙ በሲኦል ውስጥ ለጠየቀው እገዛ በመሀላችን ገደል አለ እንዳለው ገደላማት፤ መተያየት እንጂ መተጋገዝ የማይቻልበት ዓለም ነው፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ አንዳች የተስፋ ፍንጣቂ አይታይም፡፡ እዚህ ላይ የገለጽኩትን መልክአ ልቡናዊ ምስቅልቅል ይበልጥ የሚያሳይልኝ የባለቅኔውን የዮሐንስ አድማሱን ግጥም የተወሰኑ ስንኞች ነሥቼ ጥቅሉን ገለጻዬን ለማጠቃለል እሻለሁ፡፡

> እሸከለኬታችን ወይ የእንባ ሸለቆ
>
> የሰው ልጅ ሕይወቱ እውነትን ሠናይትን ውበትን ደብቆ
>
> እኒህ ተመልሰው ምድረ እርስት ሲገቡ

**እመለሳለሁኝ ያኔ ነው ዕውቀቱ የሰው ልጅ ጥበቡ**

(እስኪ ተጠየቁ ገጽ 12)

**ባለቅኔው በጥበባዊ እይታው በእነዚህ መልክአ ልቡናዊ ዓለም (በእንባ ሸለቆ ውስጥ) ሕይወት፣ እውነት፣ ሠናይትና ውበት ተደብቀው ይመለከትና ቅኔያዊ ሰቆቃውን ያሰማል፡፡ እንደብሉይ ኪዳኑ ተጋዳሊ ሙሴ ሕዝቡ ከግዞት ነፃ ለማውጣት ይመኛል፡፡ ከፊት ቀድሞ ወደ ምድረ እርስት (የአዲሱ ማኅበረ ፖለቲካዊ ሽግግር) ይጓዝና መግባቱን ይጠራጠራል፡፡ ወደኋላ ዞር ብሎ የተስፋ ቃል በመስጠት እንደተጋዳሊ ሙሴ እስከ ዳግም ትንሣኤ ይሰናበተናል፡፡ የባለቅኔው ርእይ ሸለቆን የመከራ እና የውጣ ውረድ ሕይወት ማሳያ አድርጎ አቅርቦልናልና ይህ የዕንባ ሸለቆ በአደፍርስ መግቢያ ከምናገኛቸው መልክአ ምድሮች ጋር ይናበባል፡፡ በጥቅሉ ይህ መልክአ ምድር ምድረ ፋይድ ነው፤ በዕንባ ማዕበል ሁሌም የሚናድና የሚገመስ ምድር፡፡**

**ዐቢይ ነገር**

**በምዕራፍ ፲፪ መግቢያ ላይ የቀረበልን የአድባር ዋርካ አለ፡፡ ይህ የአድባር ዛፍ የአምልኮ፣ የሥርዐት ምንጭ ተደርጎ ስለ ሚወሰድ ለሕዝበ ቀዬው መሰባሰቢያ ነው፡፡ አድባር የአማርኛም የግእዝም ቃል ነው፡፡ በግእዝ "ደብር" የሚለው ቃል የብዙ ቁጥር ብዜቱ አድባር ነው፡፡ ሥርወ ቃሉ በዚህ አገባብ አመልኮ የሚፈጸምባቸውን ስፍራዎችን፣ ትልቅ ዛፍን፣ አብያተ ክርስቲያናትንና ከፍተኛ መልክአ ምድሮችን ለመግለጽ አገልግሎት ላይ ይውላል፡፡ ይህ ቃል የጥቅሉ ማኅበረሰባዊ ባህል ማደሪያ እንደሆነ እንድናስብ ፍንጭ ይሰጠናል፡፡ አባ ዮሐንስ የእነዚህ ኹሉ ሥርአቶች እጬ ሰባኪ ናቸው፡፡ ለምስቅልቅሉ ሥርዐተ ማኅበር መንገድ ጠራጊ ዐዋጅ ነጋሪ ኾነው የአድባሩን ዛፍ እንደ ዐውደ ምሕረት ቆጥረው ይሰብኩበታል፡፡ በበአሉ ግርማ ልብወለድ (ሐዲስ) ውስጥ ለዐዲሱ ሥርዐት መንገድ ቀያሽነት እንደተመረጠው ሐዲስ ሣህሌ (በፊታውራሪ ተካ ርእይ በዐዲስ ሥጋ የተገለጠው መክብብ) ትምህርት ቤትን ለመገንባት ከሥሩ ተፈንቅሎ እንዲወድቅ እንደተወሰነበት የአድባር ዛፍ እዚህ ላይ እንዲጠፋ አልተወሰነበትም፡፡አደፍርስ ውስጥ የአድባሩ ዛፍ የዐዲሱ ሥልጣኔ መጠንሰሻ ስፍራ ተደርጎ ቀርቧል፡፡ ይህም ከቅድመ አብዮቱ በፊት ሀገር በቀሉን አስተሳሰብ ከዘመናዊ ሥልጣኔ ጋር**

ለማጣመር የተደረገውን ሥር ነቀል ያልኾነውን የለውጥ ፈለግ አመልካች ነው፡፡ አባ ዮሐንስ እዚህ ላይ የምጥምቁ ዮሐንስ ትይዩ ናቸው፡፡ ለዐዲስ ሥርዐት መንገድ ጠራጊ፣ የመስሐዊት መንግሥት ሰባኪ ሆነው ታጭተዋል፡፡ በዚህ ስፍራ እንግዳ የኾነው የእርሳቸው አቀራረብ ቆም ብለን እኮ ስለምን እንዲህ ሆነ ብለን እንድንጠይቅ ይገፋፉናል፡፡ የአንዲት ካረዳ የፍቅር ደብዳቤና የአባን ስብከት ምን ያገናኘዋል? የአባስ የአድባር ዛፍ ሰባኪነት ምን አንድምታ አለው? ደራሲው አባ ዮሐንስን ለዐዋጅ ነጋሪነት ሲመለምል ፍቅርና አንድነት በቤተ ክህነት በኩል እንዲመጣ ሊነግረን ፈልጎ ይሆን? እነዚህና መሰል ጥያቄዎችን ማንሣቱ ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለተነደፈው ጽንሰ ሐሳብ ፈር ለማበጀት፣ ነገሩን አደራጅቶ ለመግለጽ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡

በነገራችን ላይ ደራሲው አባ ዮሐንስን በሰባኪነት መመልመሉ ለምስቅልቅሉ ዐለም ሥርዐት ለማበጀት ነው ብለን በይዋሁ በተነገረን ለማመን አንገደድም፡፡ ትርጓሚያችን የተሟላ እንዲሆን በቴክስቱ ኹለንተና ውስጥ በተዘሩት የነገረሰብእ ኹነቶች ላይ ሊመሠረት ግድ ይለዋልና፡፡ እንዲያውም ነገሩን ከሥሩ ብናጤነው በጉብታዎች አናት ሆነው በቅርጽ ፍርቅርቅነት ሕይወትን ከተጫኗት መኻል ሉዓላዊውን ስፍራ የያዙት እነዚሁ ቤተ ክህነታዊ ተቋማት ናቸው፡፡ በመጥምቁ ዮሐንስ አምሳያ  በኾኑት በአባ ዮሐንስ የተሰበከው ስብከት በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ ከመኾኑ ጋር ሲጣመር ባክኖ የቀረውን የተማሪውን እንቅስቃሴና ድምፅ ያስተረጕማል፡፡ በዮሐንስ ስብከት እንደ እግዚአብሔር በግ የተገለጸው መሲሕ (መራሔ መንግስት) በዳዊት ዙፋን ላይ ሳይነግሥ ወደ መስቀል ሞት እንደተወሰደ የተማሪውም እንቅስቃሴ ራሱን ለመስቀል ሞት ያዘጋጀ ኾኖ ተገኝቷልና፡፡ የአባ ዮሐንስ ስብከት በስሜት ቀስቃሽ ቃላት ታጅበው በመኻላቸው የሻጧት ቃል ብትኖር "አንድነት" የምትለዋ ቃል ናት፡፡

> "…….አንድነት ነፃነት ነው፤ ነፃነት አንድነት ነው:: አንድነት አገር ፤አገር አንድነት ነው:: አንድነት መንግሥት ነው፤መንግሥት አንድነት ነው:: ሥልጣኔ አንድነት ፤አንድነት ሥልጣኔ ነው:: ሕይወት አንድነት ነው፤ አንድነት ሕይወት ነው:: ኀይል አንድነት፣ አንድነት ኀይል ነው:: እንኪያስ የሀገር ማኅተሟ ከተበጠሰ የሕዝብ እምነቱ ከጐደለ የሀገሪቱም ሕዝቡም አወዳደቃቸው አያምርም ማለት ነው…… "…….አገር አንድነት ፤አንድነት አገር ነው:: አለበለዚያማ አገር አገር አይሆን፤ውሃው ይመራል--- እህሉ ያንገፈግፋል---- ዓየሩ ይጐመዝዛል-መሬቱ እንደ ረሞጫ ያቃጥላል___ የሣር የቅጠሉ

> ሽታ ይመርዛል__ ሽዋ ሽለቆው ይከብዳል፤ያቃዋላል ያስጠላል__ ተራራ ሽንተረሩ ያንሽራትታል ያዳልጣል__ ነዋሪውም እንደ አይጥና እንደ ድመት እንደ ተኩላና ፍየል ተፋጦ ዕድሜውን በሙሉ ድንግጥ ድንግጥ ፍርግግ ንቅል ንቅል ትክል ትክል ሲል ነጠላ ትከሻ ሆኖ የተጠራበትን ምድራዊ ኑሮ በሕልም ሩጫ በገደል ማሚቶ ዘዬ ይጨርሳል...... ( አደፍርስ ገጽ ፣ 80-82)

አንድነት የምትለዋን ቃል እዚህ ላይ ስሜታዊ ቃላት ከበው ስለያዟት ብሶትና ስሜትን ተከትላ ትተረጐማለች እንጂ የገዛ የራሷ ትርጕም የላትም፡፡ ቅሉ አባ ዮሐንስ ራሳቸው የሚሰብኩት የስብከት ቃል አይደመጣቸውም፡፡ የስብከቱ ቃል ወደ ምድረ በዳ አስተጋብቶ ወደ ጆሯችን ሳይደርስ፣ ፍሬዋ በለኖሳስ የምታነበው የፍቅር ደብደቤ ድምጸት መልሶ ያስተጋባል፡፡ ጆሯችንን የቱንም ያህል ብንቀቅር አንድም ድምፅ ጥርት ባለ መልኩ አይደመጠንም፡፡ ድምጸቹ እርስ በእርስ ተሳክረዋል፡፡ በላይ ለፍሬዋ የጻፈላት የፍቅር ደብዳቤ ከየመንገዱ የተለቃቀሙ ትርጕም አልባ ቃላት ኹነው እናገኛቸዋለን፡፡ የፍቅር መንፈስ ስበው አያቀርቡም፡፡ ፍቅረና አንድነትን እንደ ካባ አይደርቡልንም:: መስባሰባችን ፣የአንድነት ቃለ ምዕዳኑና የትምህርት ቤት መዋጮው የመንፈስ ጎጆችንን አይሠራልንም::

> "እስከ ዛሬ ድረስ በተስፋ የቆህ
>
> ሁነው ልቤ ባሕር መስከረም ይጥባልህ" (ገጽ፣78)

ይህ በላይ ለፍሬዋ የጻፈላት የፍቅር ግጥም አንዲት ሴት አፍቃሪ ለጓደኛ የገጠመችው ቃል ግጥም ነው፡፡ በላይ መጣፉን እንጂ ለማን እንደሚጥፍ ያጤነ አይመስልም፡፡ ግጥሙ ፍቶትን ጠቅሶ ይጠራል እንጂ የፍቅርን መንፈስን ጠቅሶ አያመጣም፡፡ እኛም ለአንድ አፍታ ከፍሬዋ ጋር በፍቅር ዓለም ለመገናኘት እንጓዝና በቅጽበት ወደ አባ ዮሐንስ የአድባር ሥር ዐውደ ምሕረት እንመለሳለን፡፡ አንዱንም ዓለም በቅጡ ማጣጣም አይቻለንም፡፡ አባ ዮሐንስ "የሥልጣኔ ኩርንችት... የተመረዘ ወጣትነት... ከግብ የሚደርሰው በአንድነት ነው" (ገጽ 78) ይላሉ:: በዐዋጅ ነጋሪ ጥሪያቸው የስብከታቸውን ዶፍ ያወርዱታል፡፡ ግና አባ ለኩርንችቱ ለተመረዘ ወጣትነት አንድነት እንዴት መድኃኒት እንደሚሆን? አንድነት እንዴት እንደሚገኝ የሚሉን አንዳች ነገር የለም፡፡ ጉዳዩን ለሰሚው እንደ ዕዳ ወዝፈው ይተውታል፡፡ ይህንን ዕዳ አወራርደን ሳንጨርስ ፍሬዋ ወደምታነበው የፍቅር ደብዳቤ እንሳባለን፡፡

"ዓይንሽ የሚመስለው የብር ጉልላት

ጥርስሽ የሚመስለው የበረዶ እንብርት" (ገጽ፣ 79)

ይህንን የፍቅር ግጥም ስናጤነው የእሳቤ ቅንጅት የሌለው የስንኝ እንዝልዝል ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የብር ጉልላት እና ዐይን ለማነጻጸር ብንሞክር የሚከሰትልን ምስል የለም፡፡ የበረዶ እንብርት ብንፈልገው የትም ስፍራ አይገኝም፡፡ ይህ ደግሞ በቋንቋ አማካኝነት የተገለጠ ምስቅልቅል (ባቢሎናዊ) ዓለም ፍቅራዊ ኩሸት መኾኑ ነው፡፡ የእሳቤ ቅንጅት ሳይኖረን በስመ ፍቅር ወአንድነት እየነጎድን መኾናችንን ይጠቁማል፡፡ አባ ዮሐንስ የሚሰብኩትን ስብከት ያነብንቡ እንጂ ቅሉ ትርጒሙ ለራሳቸው እንኳን አልገባቸውም፡፡ቅሉ ይህንን ሐቅ ባይረዱትም ከድብቅ የአእምሮ ክፍላቸው በአንደበታቸው መራር ሐቆች አፍትልከው ይወጣሉ፡፡ "መጐሳል በአያት በቅድመ አያት ዘመን በተሠራ የዘር ግፍ… የኃጢአት ዋጋ በመሆን ተለውጦ ሲያራርቅ ሲያመናጭቅ ይኖራል" (ገጽ 79)ይህ በአባ ዮሐንስ የተነገረ ትንቢት አከል ዲስኩር የአንድነት ስብከታቸው ማእከላዊ ነጥብ ነው፡፡ አባ ዮሐንስ እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ለሐዲስ ኪዳን (ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ) ከብሉይ ኪዳን (ከዘመነ ፍዳ) መሸጋገር ዐዋጅ ነጋሪ መንገድ ጠራጊ ተደርገው "በፕሮግራማዊ ጽሑፍ" አፈጉባኤነትን ተሹመዋል፡፡ ስለዚህ የየዘመናቱን ኃጢአት እና በደል እየናዘዙ በንስሐ እንዲያጠምቁ ተክነዋል፡፡ ዳሩ ግን ስብከታቸውን አዳምጦ የሚናዘዝ ሰው የለም እንጂ፡፡ በእርግጥ ስብከታቸውን በአግቦቡ ካጤነው መኻል ላይ ከተሻጠችው አንድነት ከምትለዋ ቃል በቀር የግል አስተያየቶች፣ ተጨባጭ ያልሆኑ አገላለጾች የበዛበት ነገረ በክ ዲስኩር ይበዛበታል፡፡ ይህ ደግሞ ይኹነኝ ተብሎ የተደረገ ነው፡፡ ከቀዳማዊ ምስቅልቅል ወደ ዳግማዊ በቋንቋና በሓሳብ መጣረስ ዓለም መድረሳችንን ይጠቁማል፡፡ የፍቅሩም ኾነ የአንድነቱ ዓለም እርስ በእርሱ የተጣረሰ ነው፡፡"አንድነት ነፃነት ነው ነፃነት አንድነት ነው…" አባ ይባስ ብለው ቃላት እየለዋወጡ በቃላት ይጫወታሉ፡፡ ለሚያዳምጣቸው ሰው ስለ አንድነት አንዳች መረጃ ወይም ማስረጃ አያቀብሉም፡፡ የቃላቱ ጋጋታ ነገር ማክበጃ ነው፡፡ የአባ ሁኔታ ያሳዝናል፡፡ ደጋግሞ ቢናገሩም ሓሳባቸውን በግልጽ ማስጨበጥ አልቻሉም፡፡ ከዚያ አባ እንደ ነቢይነት ይቃጣቸውና አንድነትን ማጣት የሚያስከትለውን ጉዳት ያብራራሉ፡፡ "እንኪያስ የሀገር ማተቧ ከተበጠሰ የሕዝብ እምነቱ ከነደለ አገሪቱም ሕዝቡ አወዳደቃቸው አያምርም" (ገጽ 79)

አባ እንደ አዋጅ ነጋሪ ሰባኪነታቸው የቅርቡና የሩቁ ይታያቸዋል፡፡ የሀገር ማተብ ሲበጠስ የሕዝብ እምነት ሲጎድል፣ ሀገር እና ሕዝብ ሲወድቁ ይመለከታሉ፡፡ ከዚያም ግብአተ መሬት እንደፈጸመ ቀባሪ የመርዶ ያህል የከበደ ቃል ይነግሩናል፡፡ በዚህ ኹሉ ኹነት ውስጥ በለኖሳስ በቀረበው ጣዕም አልባ ፍቅር ድምፅና በምድረ በዳ በሚያስተጋባ ሰሚ ያጣ ስብከት ጥምርታ የዓለሙ ባዕድነት ተነግሮናል፡፡ አባ ባገኙት አጋጣሚ የስብከታቸው ማዳመቂያ አድርገው አንድነትን ደጋግመው ቢጠሯት አቤት አትላቸውም፡፡ የፍቅሩም ድምፅ አንድነትን ስቦ አያቀርበውም፡፡ የአንድነት ድምፅም ፍቅር ወዳለበት ስፍራ አያስተጋባም፡፡ እንደሄደ በዚያው ይቀራል፡፡ አባ በአንድነትና በነጻነት መኻል ትስስር ሊፈጥሩ ይሞክራሉ፡፡ ግና ከነቢብ ወደ ገቢር ኼደው ሲያዩት ፍሬ አልባ ይኾንባቸዋል፡፡ በፍጻሜ አባ የአንድነት ትርጉም ይሰወርባቸው እና በሌሎች ዘንድ ያለው ልዩ ትርጉም ይታሰባቸዋል፡፡ እንግዲህ እንዲህ ዐይነቱን ትርጉም ከመዝገበ ሕይወት እንጂ መዝገበ ቃላት በማገላበጥ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡ ሰሚ ማጣታቸውን ተከትሎ ልዩ ትርጉም ይታሰባቸውና ደዌው ይጣማቸዋል፡፡ በዚህም ጊዜ ያ የዐዋጅ ነጋሪው ድምፃቸው በኹሉ ሥፍራ ያስተጋባል፡፡ "ተራራ፣ ሸንተረሩ ያንሸራታል፣ ያዳልጣል ነዋሪው እንደ አይጥና ድመት እንደ ተኩላ እና ፍየል ተፋጦ ዕድሜው በሙሉ ድንግጥ ድንግጥ… ኑሮውን በሕልም ይጨርሳል፡፡" (ገጽ፣ 82) ይህ የአባ ሰቆቃወ ኢትዮጵያ በዕንባ የሚዜም እመቤቴ ተመለሽ ያለበት የተማኅፅኖ ጸሎት ነው፡፡እስኪ ደግሞ ከሰቆቃወ ሕዝብ ወደ ፍቶታዊ ፍቅር ግጥሞች እናምራ:: የከሰመውና ከሰመነው ፍቅር ፋፍቶ እናገኘው ይኾን:: ፍቅሩ በላይ ኹኖ ግርማ ሞገስ ኹኖ ያከብረን ይኾን ወይስ ምንልባት ፍቅራችን ከአበባ ወደ ፍሬ ይሸጋገር ይኾን?

ጣርማ በርላይ ሆኖ ይታያል ራሳ

ሥራው ባይሆን ይቅር እንዴት አንቺን ልርሳ::

ጣርማ በር ላይ ሆኖ ይታያል ማንያንባ

እኪሴ ላድርግሽ ቀንጥሼ እንዳበባ….

ታነባለች ፍሬዋ ከንፈሯን ያለማንቀሳቀስ::(ገጽ፣83)

የፍቅሩ ደብዳቤ እና የአንድነት ስብከት በተለዋዋጭነት መቅረባቸው ለተመሰቃቀለው ዓለም ሥርዐት ለማበጀት ነው፡፡ ይኹን እንጂ ይህ ዓለም የተፈጥሮ ያህል ጸናን የሆነ ሞትና

መከራን የሚጠራ ዓለም ነው፡፡ በዚህ ዓለም ውስጥ የሰውነት ደረጃ ወደ አውሬነት ወርዶ በፍርሃት ይተበተባል፡፡ ለዚህ ኹሉ መንሥኤው ማኅበረ ፖለቲካው ፍቅርና አንድነትን አይሰብክም ቢሰብክም በነቢብ እንጂ በገቢር አያውቃቸውም፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ሰብኣዊ አእምሮና አካል ሥራውን በአግባቡ አያከናውንም፡፡ የዜጎች ጉልበት በዘፈቀደ በጥላቻ እና በፍርሃት ይባክናል፡፡

“….እንዲህ ካልሆነ ግን ከሰው የባሰ አውሬ የለምና፣እራሱን እንኳ ለመግደል የመማይመለሰው ፍጡር….ሌላውን ቀርቶ ጌታ የሱስ ክርስቶስን እንኳ እንደገና ተወልዶ ቢመጣ__ ዓላማውን የሚያሰናክልበት ሆኖ ካገኘው__ ይሁዶች ካሠቃዩት የበለጠ አይሠሩ ሥራ እንደሚሠራው አያጠራጥርምታዲያንን ይህን የሰውነት አውሬነት እንዴት ማስወገድ ይቻላል…?አንድነት ኀይል ኀይል አንድነት መሆኑን በማስገንዘብ ነዋ! እያንዳዳችን በዚህ ጐዳና በመምራት ነዋ! ምናልባት!ምናልባት! አንድነት ኀይልን ተሸክሞ ከጐዳናው አፍንጫ ላይ ብናገኘው….”(ገጽ፣84)

አባ ዮሐንስ በፍጻሜ በደመነፍስ ምርጫ ቢሆን የሚያቀርቡል አማራጭ አለ፡፡“ወገን እና ጐሳ የሚባሉትን እንክርዳድና መጭ ነቅለን በመጣል… አንድነትን መርጠን እንቀናጅ፡፡” (ገጽ 84) አባ ዮሐንስ በዚህ ርእያቸው መሠረት የጻድቃን ሀገር መፍጠር ይመኛሉ፡፡ አባ ሀገርን እንደ እርሻ ተመልክተዋልና፡፡ “ስንዴ” እና “እንክርዳድ” አብረው መብቀላቸውን መቀበል አልፈለጉም፡፡ “የአጨዳው ወራት እስኪኾን አብረው ይደጉ የሚለው የወንጌል ቃል አልታወሳቸውም” ተዘክሯቸውም እንደ ተመሰቃቀለው ዓለም እብሎ አይታዘዛቸውም፡፡ በእርግጠኝነት አንድነት እንዳልሰበኩ ሁሉ “ማን ያውቃል? ይሠራ እንደሆን? ማን ያውቃል?...” በማለት በጥርጣሬ አዘቅት ውስጥ ይሰጥማሉ፡፡

“…… የጀግነት ሥራቸውን አሳይተው፣ ቅርስ አሳልፈው፣ የረገፉባት __ የአካል እናታችን አለኝታችን፣ መሸሻችን፣ መሸሸጊያችን ነች ማለት ነውና__ ወገንና ጐሣ የሚባሉትን፣ እንክርዳድና መጭ ነቃቅለን፣ በመጣል__ በየልባችን የጠቀረሸውን የነገር እርሾ ለቅልቆ በማፍሰስ፣ የሕይወት አክሊል የሚሆነውን አንድነትን መርጠን፣ በመቀዳጀትና በእርሱ ሥር በመራመድ__ ምናላባት ልንከላከለው እንችል ይሆናል:: ማን ያውቃል? ምናልባት ይሠራ እንደሆን? ማን ያውቃል የግባችን ቀጥታ መሥመር እንደዚህ እንደሆን? ማን ያውቃል….?( ገጽ፣83)

የአባ ማን ያውቃል?ተስፋና ቀቢጸ ተስፋን ባንድ አንቅልባ ያሳዝለናል፤ቅሉ እሽሩሩው ቢደክመንም::አባ እዚህ ስፍራ ሲደርሱ ተክኖቸውን ነጥቀዋል፤የምድሩ እንጂ የሰማዩ አይታያቸውም::እንዲህም ይኹን እንጂ መተግበሩ ቢያዳግትም ምክር ብጤ ይለግሱናል::

"…ለማስተባበር የሚቻለው ማጣትም ማግኘትም መደሰትም ማግኘትም አንድነት ሲሆን ነው:: ነፃነትና አንድነት መንትዮች ናቸው:: … እንዲህ መሆናቸውን ዐውቀን ልሠራባቸው ያስፈልጋል:: እንዲህ ካልሆነ ግን ነፃነት ያልታወቀ ትርጉም ይኖረዋል ማለት ነው:: ምናልባት ይትርጉም ያልታቀው ትርጉም ለጥቂት ሰዎች እንጂ ለብዙዎች አልተገለጸ ይሆናል:: ምናልባት ለብዙዎች ሲገለጽ በሽታ ይሆን ይሆናል:: ምናልባት እንደማር በጥቂቱ እንጂ ሲበዛ ይመር ይሆናል:: ምናልባት ይህ ልዩ ትርጉሙ እየታወቀ አያናግር፣ አያሠራ፣ አያበረታታ፣ ደዌውን ተክሎብን ይሆናል__ ምናልባት ማንውቃል…." ያስተጋባል ያባ ድምፅ ከጋራ ጋራ::(ገጽ፣82)

አባ የምንሠራባቸው የምናስተባብራቸውን ግብራት ይነግሩናል፤አዳማጭ ግን ያላቸው አይመስልም ነፃነትን ከአንድነት ጋር ማጣትን ከማግኘት በአብሮነት እንድንጋራ ይመክሩናል::ትርጉም ከተርጓሚው እንጂ ከነገሩ እንደ ማይገናኝ ይታሰባቸዋል:: ኹኔታው ያልታወቀ ትርጉም ፣በሽታ ፣የሚመርና የማያናግር ደዌን የሚተክል ኹኖ ይታያቸዋል::በዚህ ቅጽበትነው ድምፃቸው በኹሉም ስፍራ የሚያስተጋባው:: ከራሱ ከዳኛቸው ወርቁ "እንቧ በሉ ሰዎች" ከሚለው የግጥም መድበል ይህን ሐሳብ የሚያጎላ የሥንኝ ቋጠሮ ወስጄ ለእሳቤው አጽንዖት ልስጥ::

እኔ እንደ ሚመስለኝ

እንደ ጆሮ አንቀርም

እንደ ቀንድ አንሾርም

በሻኛ አንገታም

እንደ ራስ ላነቃ እንጂ

እንደሳት አንሆንም፤

የወንድ አገር ይዘን

የአባቶች ድግ ታጥቀን

በባህል ተወረን__

መጥፎ ስም አንግሠን

ጥሩ ስም አንቀብርም

አገራችን ለእኛ ዕድላችን ለእኛ

ታራሚዎች እኛ ታዳጊዎች እኛ::

.......................................

አይ እኔ አይመስለኝም

እንዲህ አልታየኝም

ግና ማን ምን ያውቃል

እንኖር ይሆንል፣

እንኖር ይሆናል ጭራ ቀረሾች

ልባዊ ሰይጣኖች ገጻዊ ሰዎች

እንኖር ይሆናል:: (እንቧ በሉ ሰዎች ገጽ፣61) ዳኛቸው ልባዊ ስጋቱን ውስጣዊ ፍርሃቱን በእነዚህ የሥንኝ ቋጠሮዎች አካፍሎናል:: አንዴ በርግጠኝነት ይመስለኛል ሌላጊዜ አይ እኔ አይመስለኝም በማለት የነገሩ እስባታይነት ያወጋናል:: የወንድ አገር ይዘንና የአባቶች ድግ ታጥቀን ይታየውና ብርታት ይሰማዋል:: በዚሁ ቅጽበት በጋራ ታራሚምና ታዳጊ ኾነን አይቶ ደስ ይለዋል:::: አገራችን ዕድላችን ሠምረውና አብረው ይመለከታል፣ ወጤቱም መጥፎ ስም አንግሦ ክፉ ስምም አለመቅበር መኾኑ ይረዳዋል:: ይህ ስሜቱ ግን አይዘልቅም በቅጽበት ጥርጣሬ ይጣባዋል:: ዐዲስ ራእይ ይገለጥለታልና አይ እኔ አይመስለኝም ብሎን ወደ ጥርጣሬ አዘቅት ይወስደናል::

የመጻኢው ዘመን ኅግማንጉኅች፣ ጭራ ቀረሾቹ፣ ላባዊ ሰይጣኖቹ ገጸሰቦች ይታዩታልና።ይህ ድቅድቅ ጨለማ ነው፤ለፍቅር ግጥሙና ለአንድነት ስብከቱ ያለመሥመር ጠንቅ የሚኾ ነው። አባ በስብከታቸው ፍጻሜ ዋና ነገር (ገንዘብ ማሰባሰቡን) ረሳሁት በሚለው ንግግራቸው "አንድነት" ወሬ ማሳመሪያቸው እንጂ ዋና ጉዳያቸው እንዳልኾነ ራሳቸው ተናግረውታል፡፡ የአባን ስብከት አቶ ጥሶ (ተራማጅ ኢትዮጵያዊ ገጸ ሰብእ) በሚመለከተው መልኩ ገልጸውታል፡፡ "አላስጨረስከኝም እኮ!አስጨርሰኝ__ የሃይማኖት አፋዳሽ ደግሞ አለ..."እንደ ጧቱ እንደ አባ ዮሐንስ ዓይነት...!" ያቋርጣቸዋል እንደገና አደፍርስ።(ገጽ፣86) በአቶ ጥሶ ተሐዝቦት መሠረት የአባ የአንድነት ስብከት በማወቅና በመረዳት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ከንቱ ማፋደስ ነው፡፡ በፍጻሜ ፍሬዋ የተጻፈላት ደብዳቤ ውሃ እየቀዳችበት መጫወቻ እንደደረገችው ተገልጾልናል፡፡

ፍሬዋ በተጣፈላት ደብዳቤ ውሃ እየቀዳች ትጫወትበታለች...ሁለት ሦስቴ ስትዘግንበት ጽሑፉ ይደመሰሳል...ወረቀቱ ከእጇ ላይ መብሰክሰክ ሲጀምር__ጭራሹኑ ውሃ ላይ ትለቀዋለች፤ሳግ__ሳግ__ሳግ__ስጐ ሲያበቃው ቁልቁል__ ይመነጠቃል፡፡(ገጽ፣85)

ይህ ድርጊት በዚህ ምስቅልቅል ዓለም ውስጥ ፍቅር አንድነት ዋጋቢስ መኾናቸው ጠቋሚ ነው፡፡ ለዚያም ይመስለኛል ፍሬዋን የመሰለ ልባም ልጅ የፍቅር ውዳሴው ዝባዝንኬ ኾኖባት ውሃ እየጨለፈችት የምትጫወትበት።አደፍርስን በሞገተ ርቱዕ አንደበት፣ መጻኢውን በሚያጤን የላቀ ልቡናዋ ላይ ፍቅራዊ ግጥሙ ተጽኖ ማሳደር አልቻለም። ይህን ሐሳብ ይበልጥ የሚገልጽልኝ የባለቅኔው የዮሐንስ አድማሱን የተወሰኑ ስንኞች በመውሰድ ለሐሳቡ አጽንዖት ልስጥበት፡፡

ፍቅር ይጥፋ ይውደም

ይቅር ኑሮ

ይጥፋ ኑሮ

ይውደም ኑሮ

ፍቺ አልባ ፍሬ አልባ ተዘርሮ፡፡

.......................................

ያለም እውነት ያለም ሥራት፣

እነዚህ ሁሉ ጠፍተው ሁነው ምስቅልቅል
አለመኖር ገብተው ቢኖሩ በእድል
(እስኪ ተጠየቁ ገጽ፣ 72)

በባለቅኔው ፍቅርን አልተዘመረለትም፡፡ ፍቅር እና ኑሮ ከህላዌ ውጭ ተደርገዋል፡፡ ፍሬ አልባ እና ዋጋ ቢስ ኾነዋል፡፡ በማሳያነትም ምስቅልቅልነታቸው ተጠቅሷል፡፡ ይህ የባለቅኔው ገለጻ በአደፍርስ ውስጥ ከተገለጠው ፍቅር እና አንድነት ከተሰደዱበት ዐለም ጋር ተናባቢ ነው፡፡ በፍጻሜም እኛ ጋር የሚቀረው የአንድነትን ደምፅ የሚያስተጋባ የገደል ማሚቶና ተብሰክስኮ ቁልቁል የሚመነጠቅ ፍሬ አላባ ፍቅር ነው:: አለመኖርና ምስቅልቅል የሰፈነበት ፍቺ አልባው ኹነት የዚህን ዓለም ጽንት በምልዐት ይገልጻል፡፡

## ማጠቃለያ

ዳኛቸው ወርቁ በድርሰቱ ውስጥ በተዘሩት የነገረ ሰብእ እሳቤዎች የምስቅልቅሉን ገጽታ በማኅበረሰቡ አቋመ ባህል ሥግው አድርጎ አቅርቦልናል፡፡ የአደፍርስ እና የጽዮኔ፣ የፍሬዋና የአቶ ጥሶ አቀራረጽ የዚሁን ዓለም ውጥቅጥቅ አመላካች ነው፡፡ በሌላ መልኩ የወይዘሮ አሰጋሽ፣ የአቶ ወልዱ፣ የእነጎርፉ ዓለም የዚሁኑ ዓለም ጽነትን ፈካሪ ነው፡፡ በፍሬዋ የፍቅር ደብዳቤ እና በአባ ዮሐንስ የአንድነት ስብከት የዚህ ዓለም የፖለቲካ አማራጭ (ፍቅር እና አንድነት) እንደኾነ ተገልጧል፡፡ ይሁን እንጂ በተመሰቃቀለው ዓለም ውስጥ ምንም ተስፋ ሰጪ ጭላንጭል አልቀረም፡፡ በፍጻሜ ፍሬን ከንስሐ፣ ፍቅርን ከአንድነት በማጣለፍ በርእዮተ ዐለማዊ አተያይ አዋቅሮ አንድነትና ፍቅርን ስብከትም ግጥምም አድርጎ አመስጥሮ የያቀረበል ብዕር ትብ ነው፡፡ በዚህም ምስቅልቅል ዓለም ለመቤዠት ለመዳን የቀረልን ረጀት ፍቅር ወአንድነት ነው፡፡ የነገሮቹ ኹሉ መቋጫ የምስቅልቅሉ ሥርዐት ማብቂያ፡፡ በዚህ መልኩ ፖለቲካዊ ርእይ በኪናዊ ሥራው በረቀቀ መንገድ ሥግው ሆኖ ቀርቧል፡፡በድርሰቱ ውስጥ የቀረበልን ዓለመ ሰብ አስቂኝ ነው:: ከየአቅጣጫው ጭኸት ያስተጋባል፤ ያአንዱም ድምፅ ጥርት ብሎ አይሰማም፡፡ የኮረዳዋ የሉኖሳስ ግጥም፣የአባ ስብከትና የገበሬው ፉጨትና ቀረርቶ ተደባልቋል፡፡ በድምፃዊው ባቢሎን ፍቅርና አንድነት ቀዬውን ለቀው ተሰደዋል፡፡ድርሰቱ የዚህ ክቡድ ራእይ ሠረገላ ነው፡፡

## ዋቢ መጽሐፍት

ታሪክነህ አጥናፉ፤1970፤"የዳኛቸው ወርቁ የአጻጻፍስልት በአደፍርስ"፤ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል የቀረበ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ::

ቴዎድሮስ ገብሬ፤2001፤በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ጥበብ፤ አዲስ አበባ፤ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፡፡

_________ ፤2006፤"አደፍርስ ዘመናዊ ልብወለድ" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነጽሑፍ መጽሔት፤ቁጥር1-2፤የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ገጽ119-150::

አምሳሉ አክሊሉ፤1976፤"አጭር የኢትዮጵያ ሥነጽሑፍ ቅኝት"፤(ያልታተመ)አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ::

ኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር፤ 1980፤ መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይ ኪዳን እና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፡፡

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፤ 1984፤ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዮሐንስ አድማሱ፤ 1990፤ እስኪ ተጠየቁ፤ አዲስ አበባ፤ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ዳኛቸው ወርቁ፤ 1962፤ አደፍርስ፤ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

___________፤የጽሑፍ ጥበብ መምርያ፤1977፤አዲስ አበባ ፣ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

__________፤እንቧ በሉ ሰዎች፤1967፤አዲስ አበባ፣ብርሃንና ሰላም ማተሚያቤት::

ፈቃደ አዘዘ፤1990፤"የገለጻና የምልልስ ፋይዳ በአደፍርስ የመጀመሪያ ምዕራፍ"፤የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነጽሑፍ መጽሔት፤ቁጥር 8፤የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፤ገጽ1-24::

Cavallaro, Dani. 2001. Critical and Cultural Theory. New York and London: The Athlone Press.

Durant, Will. 1954. The Story of Philosophy New York: Simon and Schuster Center. `